



www.ethiopianorthodox.org

የጀት ሬታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

7/07/1974

# ች ግ ጺ ዓ ዮ

« አስቀድሞ የእ
ግዚአብሔርን ስም
የጠራ ሁሉ ይድናል »
(የሐ· ሥ· ፪· ፳)


«ጸልዩ ትጉም
ወደመከራ እንዳ
ትገቡ»
(ማቴ· ፳፮· ፵፩)

ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅ ነህ

አ· አ· ፲፱፻፶፰ ዓ· ም·

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በሠላሳ ስድስተኛው ዓመተ መንግሥት ፲፱፻፶፰ ዓመተ ምሕረት ይህ መጽሐፍ ታተመ



ዕቀብ ንግሦ ወሠራዊቶ ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ

www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ


| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም ........... | 5—16 |
| መግቢያ ............ | 17—19 |
| የጸሎት ሥነ ሥርዐት.......... | 20—23 |
| የጸሎት አስፈላጊነት.......... | 23—25 |
| መቼ መጸለይ እንደሚገባ ..... | 26—34 |
| ወዴት መጸለይ » ...... | 34—44 |
| ለባልንጀራ መጸለይ » ...... | 44—47 |
| ስንጸልይ እንዴት መሆን እንደሚገባን | 47—53 |
| የጸሎት ዐይነት .......... | 53—56 |
| የጸሎት ጥቅም .......... | 56—60 |
| ማጠቃለያ .......... | 60—68 |


www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

ጸሎት ማለት የእግዚአብሔርና የሰው
ልጅ ግንኙነት የሚገለጥበት ፤ ሰው እግዚአ
ብሔርን የሚያነጋግርበት ቋንቋ ፥ እግዚአብሔ
ርም የሚገኝበት መንገድ ነው ፤ ምክንያቱም
ሰው በጸሎቱ ፥ በልመናው ፥ በምስጋናው
እግዚአብሔርን በቃል ያነጋግረዋል ። እግዚአ
ብሔርም ደግሞ በቸርነቱ ብዛት ከባሕርዩ
የሚመነጩትን የርኅራኄ ሥራውን በማድ
ረግ ፥ ግዳጁንም በመፈጸም ፥ ልመናውን በመ
ስማት በጠቅላላም በታላላቅ ሥራው ይመል
ስለታል ። በጸሎታችንም ታላቅነቱን ፥ ከፍተ
ኛነቱን እንገልጣለን ፤ እንዲሁም ትሕትናውን ፥
ቸርነቱን እናደንቃለን ። ምስጋናውንም ገል
ጠን እንመሰክራለን፤ እንዲሁም ያለንን ስሜት
ሁሉ ችግራችንን እናዋየዋለን ፤ እንለምነዋለን።

ስለ ምስጋናው በሰማይ ያሉ ረቂቃን ፍጥ
ረቶች ሰማያትም ሳይቀሩ ፥ በምድርም ያሉ

www.ethiopianorthodox.org

ግዙፉን ምድር ሳትቀር ያመሰግናሉ፤ « ሰማዮች የአምላክን ምስጋና ይናገራሉ ። የሰማይም ጠፈር የእጆቹን ሥራ ያወራሉ » ( መዝ/፲፱ ቍጥር ፩) ሲል ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል ። በተለየ ግን ሰው የተፈጠረ ለቅዳሴ፣ ለውዳሴ ፣ ስሙን ለመቀደስ ፣ ክብሩን ለመውረስ እንደ ሆነ ፤ «ወሶበ ኢያእኰትኮ ለዘፈጠረከ እምነፋስ ወነድ፤ ፈጠረ ህየንቴከ ሰብአ ዘማሬ እማይ ወእመሬት ሲል » ያስረዳል ። ይኸን ቅዱስ ቃል አብነት በማድረግ በየሰዓቱ ፣ በየዕለቱ ፈጣሪያችንን ማመስገን ፣ በጸሎትም መነጋገር የሁላችን ግዴታ ነው ።

ፈጣሪያችን በጸሎት በተነጋገርነው ቍጥር ረቂቁ ጕልቶ ፣ ከባዱ ቀሎ ፣ ጨለማው በርቶ ፣ በጠቅላላውም ሁሉ ለኛ ግልጥ ሆኖ ይታያል ። ከእግዚአብሔር ጋራ ግንኙነት ያላቸው ከእግዚአብሔር ጋራ በጸሎት



የሚነጋገሩ ፣ ከእግዚአብሔር ጋራ አንድነት ያላቸው ሰዎች ከቶ ችግር፣ፈተና፣ድንቍርና እንደሌለባቸው«እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ለድካማችን ኀይል ይሰጣል ፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ። ነገር ግን እርሱ መንፈስ ቅዱስ ይጸልይልናል ፤ በማይነገር------ልብን መርምሮ የሚያውቅ የመንፈስንም ፈቃድ ያውቃል ። እርሱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይለምናል» ( ሮሜ ፰፣ ፳፯ -፴፩ ) ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ያስተምራል ።እንኳን ብዙ ችግርና መከራ ያለበት፣ክፋትና ኀጢአት የሚስማማው ፣ በጠቅላላም ብዙ ፍላጎት ያለው የሰው ልጅ በረቂቅ ዓለም ተውጠው፣ ጸጋውን ለብሰው ፣ ጸጋውንም ተጐናጽፈው የሚገኙ ምንም ፍላጎት የሌላቸው መላእክት ዕረፍታቸው ምስጋናቸው፣ምስጋናቸው ም ዕረፍታቸው ሁኖ ከተፈጠሩበት ዕለት ጀምሮ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ይኖራሉ።(ዜና መዋዕል ፩-፴

www.ethiopianorthodox.org

ፊል፡፬-፯ ፤ የዮሐ - ራእይ ፬ ፡ ፲፩-፲፬ ፤ ም/ ፲፱፡፮-፯ ) ስለዚህ ሁል ጊዜ የሰው ልጅ ከሰው ጋራ ከመነጋገሩ በፊት ከፈጣሪው ጋራ መነጋገር እንዲሁም ክፋትን፣ ተንኰልን ዐስቦ ወይም ተናግሮ ከመከራ ከመውደቅ ይልቅ ጸሎት ጸልዮ ጸጋን ፣ በረከትን ፣ ረድኤትንም ማግኘት የበለጠ ነው ፤ ይህንንም ታላቅ ጥቅም አውቀው ብዙ ቅዱሳን ሰዎች በሚገባ ይፈጽሙት ነበር ፤ ለምሳሌ ፣ ንጉሥ ዳዊትና ነቢዩ ዳንኤል ፣ እንዲሁም ሌሎችም ነቢያት በሚገባ ፈጽመውታል ። ለምሳሌ፣ንጉሥ ዳዊት ምኞቱ፣ ንጉሥነቱ ሳይከለክለው ፣ እንዲያውም በአስተዳደር ሥራው ላይ ሳይዘነጋ ፣ ሳይሰለች ጧትና ማታ ቀርቶ ሌሊትም ይጸልይ እንደ ነበረ «ስለ ጽድቅህ ፍርድ በኩል ሌሊት አመሰግንህ ዘንድ እነሣለሁ» (መዝ/፻፲፱፡፷፪) «አቤቱ በሌሊት ስምህን አሰብኩኝ ፤ ሕግህንም ጠበቅሁኝ ። (መዝ/ ፻፲፱፡፶፭) ሲል ያስረዳናል ።



እንዲሁም የጸለየውና የዘመረው ሁሉ ተሰብስቦ ፻፶ መዝሙረ ዳዊት እየተባለ ዓለም ሁሉ ሲጠቀምበት በመገኘቱ ምስክርና አስረጅ ሆኗል ። ነቢዩ ዳንኤልም በሰላምም ጊዜ በእስር ቤትም ሁኖ ይጸልይ እንደ ነበር እንረዳዋለን « ዳንኤልም ጀመረ አለም፤ የእግዚአብሔር ስም ለዘለዓለም ይመስገን ፤ ጥበብና ኀይል ለእርሱ ነውና እርሱ ዘመንና ሰዓትን ይለውጣል ፤ እርሱ ነገሥታትን ያፈልሳል ፤ ነገሥታትን ያስነሣል ፤ ጥበብን ለጠቢባን ይሰጣል ፤ ዕውቀትንም ለሚያስተውሉ የጠለቀውንና የተሰወረውን እርሱ ይገልጣል ፤ በጨለማ ያለውን እርሱ ያውቃል ፤ ብርሃን ከርሱ ጋራ ነውና ፤ እገዛልሃለሁ ያባቶቻችን አምላክ ሆይ አንተንም አመሰግናለሁ » (ዳንኤል ፪፡፳-፳፫ ) ሲል ጸልዩ አለ ።

ጸሎት የጠመመው ሁሉ ማቅኛ የማትነበር መሎጊያ ናት ፤ ጸሎት የሁሉን በር የምትከፍት የወርቅ መክፈቻ ናት ፤ ጸሎት ሁሉን የምታስደስት የምሥራች ናት ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ የጸሎትን ጥቅም ክርስቶስ ሲያስረዳ «ንቁና ጸልዩ ወደፈተና እንዳትገቡ »(ማር/ ፲፫፡፴፫)ቸኩሉ ፤ጸልዩም ወደፈተና እንዳትገቡ» (ማቴ/ ፳፮፡፵፩)።እንዲሁም በጸለይን ጊዜ መሰልቸት፣መታከት እንዳይገባን በጨካኙ ገዥና በደጀጠኝዋ ድሀ መስሎ ተናግሮአል። (ሉቃ/ ፲፰፡ ፩-፲፬) « ባልዋጇባት እጣት የዘንዶ ጕድጓድ አይለኩባት » እንደተባለው ክርስቶስ የማይሠራውን አያስተምርምና እኛ ብቻ እንድንጸልይ አያዘንም ፤ ነገር ግን ራሱ አስቀድሞ እከብር አይል ክቡር ፤ እጸድቅ አይል ጻድቅ የባሕርይ አምላክ ሲሆን በከተማ ፥ በምድረ በዳ ብቻውንም ከተማሪዎቹም ጋራ ሲጸልይ ይገኝ ነበር እንጂ ፤ (ሉቃ/፮፡፲፪-፲፫ ፤ ማቴ/ ፲፬/ ፳፫ ፤ ምዕ፡፳፮፡ ፴፱ -፵፬ ) ከዚህም ሌላ አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ብሎ የጸሎትን ስልት ዘርዝሮ አስተምሯልና ። የርሱ ተከ



ታዮች ሐዋርያትም የሥራቸው መጀመሪያና መፈጸሚያ ጸሎት ብቻ እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል ። ለምሳሌ፥ ሐዋርያት በይሁዳ ፈንታ ማትያስን ሲሾሙ ጸለዩ፤ ( የሐዋ/ ሥራ ፩፡፳፬፡፳፮)፤ ማዕርገ ክህነትን የሐዋርያነትንም ማዕርግ ሲሰጡ ይጸልዩ ነበር ( የሐ/ ሥራ ፲፫፡፪—፫) ።

በተለይ ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቶስን ትምህርት ተከትሎ ራሱም አዘወትሮ ይጸልይ ነበር፤ሰውም እንዲጸልይለት ይለምን ለሰውም ያስተምር ነበር ። ለምሳሌ ፡ ተወዳጅ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን « እኔም እመክርሃለሁ ከሁሉ በፊት ልመና ፥ ጸሎትም መማለድም ፥ ምስጋናም ስለ ሰው ሁሉ እንዲደረግ ፤ ስለ ነገሥታት ፤ ስለታላላቆችም ሁሉ በሕይወታችን እንኖር ዘንድ ፤ በጸጥታና በሰላም በመልካም አምልኮ ሁሉ በቅንነትም » (፩ኛ ጢሞ/ ፪ ፡ ፩—፪)

www.ethiopianorthodox.org

ጸሎት የምሕረት በር መክፈቻ ናት ፤ ማለት ያጣ ሲለምን ያገኛል ፤ የተቸገረ ግዳጁ ይፈጸምለታል ፤ የታመመው ይፈወሳል ፤ የደከመው ይበረታል ፤ የደኸየው ይበለጽጋል ፤ ደንቆሮው ዐዋቂ ይሆናል ፤ በዚህም ሁሉ ምክንያት ጸሎት የማትሰበር የሁሉ መክፈቻ ናት ለማለት ይቻላል ።

አንድ ሰው ሁል ጊዜ ጠንክሮ ቢሠራም ጸሎት ካልጸለየ የሠራሁትንም ባርክልኝ ብሎ እግዚአብሔርን ካለመነው የለመነውንም እንደሚሰጠው ካላመነ የሥራውን ፍሬ ሊያይ አይችልም ፤ ውጤቱን ያጣል ፤ ለምሳሌ ገበሬው ሳይጸልይ እንዲሁ ቢዘራው አንበጣ ይበላበታል ፤ በረድ ይመታበታል ፤ ድርቅ ያስቀርበታል ፤ ነጋዴው ሳይጸልይ ፣ ሳይለምን ቢሠራ ወረቱ ይጠፋበታል ፤ ትርፉ ያንስበታል ፤ ገቢያው ይሰበርበታል ፤ ወታደርም እንዲሁ ከሥራው ጋራ እግዚአብሔር እንዲሆንለት ፣ የሚሠራውን ሥራ እንዲባርክለት ካልጸለየ



ጠረፉንም ካልጠበቀለት አንተ ከኔ ጋር ሁንልኝ በአንተ አምኜ የምሠራው ሁሉ ቅዱስ ፈቃድህ ይደረግልኝ ብሎ ካልጸለየ ሌሊት በቍር ፣ ቀን በሐሩር የሚጠብቀው ሁሉ ከንቱ ነው ።

ጌታ አገርን ካልጠበቀ ጠባቂዎች ወታደሮች በከንቱ ደከሙ፤ (መዝ ፻፳፮፡፩) ሲል ነቢዩ ዳዊት ያስጠነቅቃል ። ብዙ ሰዎች ቅን አገልጋዮች ፣ ታማኞች፣ሠራተኞች ሲሆኑ የሚሠሩት ሁሉ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና ያለ ጸሎት ስለማይሆን ዋጋቸውን ሳያገኙ የቀሩ፣ በዕድላቸው ሲያማርሩ የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው ።

ስለዚህ ማንም ሰው በሚሠራው ሥራ ሁሉ የእግዚአብሐር ቸርነትና ርዳታ ቅዱስ ፈቃድም እንዲጨመርለት « ወይኩን ፈቃድከ » ብሎ መጸለይ ይገባል ። ብዙዎች መሐንዲሶች አውጥተው ፣ አውርደው

www.ethiopianorthodox.org

አጥንተው ለክተው ቤትን ይሠራሉ ። ነገር ግን በሥራቸው በሐሳባቸው ፥ እግዚአብሐር ሳይጨመርበት ሲቀር መሠረቱ ይናወጣል ፤ ቤቱ ይፈርሳል ፤ ማለት መሬት ይናወጣል ፤ መሠረቱ ይቀልጣል ፤ ቤቱ ይፈርሳል ። እንዲሁም ከሆነ ሁል ጊዜ በከንቱ አናጢዎች ይደክማሉ ማለት ነው ። እግዚአብሐር ቤትን ካልሠራ አጢናዎች በከንቱ ይደክማሉ ( መዝ/ ፻፳፯፡፩ ) ፡ ሲል ነቢዩ ዳዊት በምንም ጊዜና በማንኛውም ሥራ እግዚአብሐር ሊኖርበት ሊፈቅድም እንዲገባ ያስጠነቅቃል ፤ እግዚአብሐር ቤትን ካልሠራ ስንል አሁን እግዚአብሔር ራሱ ውሃ ቀድቶ ጭቃ አቡክቶ ፥ ግንብ ወይም ግድግዳ የሚሠራ ሁኖ አይደለም ። ነገር ግን ማንም ሠራተኛ በሚሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሐር እንዲጨመርበት መጸለይ እንዳለበት የሚያስጠነቅቅ ነው ። ከዚህ በቀር ክር



ስቶስ ሲያስተምር ከእኔ ወጥታችሁ ምንም ለመሥራት አትችሉም » (ዮሐ/፲፭፡ ፭-፮)ብሎ አውጇአል ፤ ይህም ማለት ርሱን እርዳን ፥ ፈጽምልን ፡ ስማን ሳንል የሠራነው ሁሉ ከንቱ ዋጋ ቢስ እንደ ሆነ የሚያረጋግጥ ነው ፤ ለምሳሌ ይኸ ኋኛው መቶ ዘመን ለኑሮ ምቾትን የሰጠ የሥልጣኔ ዘመን ነበር ፤ ግን ሁሉ ከጸሎት የራቀበት ፥ እግዚአብሔርን የረሳበት ዘመን በመሆኑ ማን ይደሰታል ፤ ደስታ የተባለው ነገር ከሰው ልጅ ርቆ ትንሹም ትልቁም ሲጨነቅ ፡ ሲያዝን ፥ ሲበሳጭ ይገኛል ፤ ምክንያቱን ስንመረምር ግን ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ራቀ ፥ ጸሎት ስለማይጸልይ እንደ ሆነ ርግጠኛነቱ ታውቋል ፤ እግዚአብሔር ያልባረከው ሥልጣኔ ወይም ጥበብ ተመልሶ ለጥፋት ሆኗል ።

ጸሎት በሥራ ሁሉ ይረዳል ፤ ማለት ማንኛውም ሥራ ያለድካም ይሠራል ፤ ወይም

www.ethiopianorthodox.org

ውጤቱ ያማረ ይሆናል ፤ ለምሳሌ ፣ በጦርነት ጊዜ ጠላትን ድል ያደርጋል ፤ ከአባር ፣ ከቸነፈር ፣ ከችግር ያድናል ፤ ለድሃ ልብሱ ፣ ጉርሱ ፣ ለባለ ጸጋ ሞገሱ ነው ። ጸሎት በጎይል የተዘጋውን የምሕረት በር የሚከፍት ጠንካራና የማይሰበር መክፈቻ ነው ። ጸሎት የራቀውን የሚያቀርብ ፣ የረቀቀውን የሚያጐላ መነጥር ነው ። ጸሎት የተሰበረውን የሚጠግን ፣ የተለያየውን አንድ የሚያደርግ ሙሻዘር ነው ። በጸሎት ስንት ሰዎች ከጎዘናቸው ተጽናኑ ? ሥራቸውንስ አከናወኑ ? በጸሎት ስንቶች ከፈጣሪያቸው ጋራ ታረቁ ? እውነተኛውን ጐዳና ዐወቁ ? ስለዚህ ሁላችን በአንድ ድምፅ ወደ ፈጣሪያችን እንጩህ ፤ እንለምን ፤ እርሱንም እናመስግን ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

# መግቢያ

ከሌላው ጊዜ ይልቅ አሁን በጣም ሁላችን የምንጸልይበት በጸሎትም ፈጣሪያችንን የምናገኝበት ጊዜ ነው ፤ ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ የሰወ ልጅ ሁሉ ፈጣሪውን የዘነጋበት ተፈጥሮወን የረሳበት ሕይወቱ አሥጊ የሆነበት ጊዜ ስለ ሆነ ነው ።

ከሌላው ጊዜ ይልቅ አሁን ልንጸልይ ይገባናል ያልኩበት አንደኛ በቀድሞ ዘመን በእውነተኛው መንገድ አይሁን እንጂ ፣ እያንዳንዱ ነገድ መስሎ ለታየው ነገር ሁሉ ይሰግድ በመሰለውም ዐቅደ ፈጣሪውን ያመልክ ነበር ፤ አሁን ግን ዕውቀት የበዛውን ፣ ሥልጣኔ የተስፋፋውን ያህል ፈጣሪን መርሳት ከእውነተኛው መሥመር መውጣት ፣ ፍቅር አንድነትን ማጣት በሰው ልጅ ሁሉ የወል ሆኖ ስለ ተገኘ ፤ ማንኛውም ሕዝብ ለጥፋት የተዘጋጀ ሆኖ ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

ወደ ፈጣሪ ተመልሶ ይቅርታ የሚጠይቅ፤ከክፉ ነገር የሚርቅ ባለመኖሩ፤ ሁሉንም ወደ ሥጋት ጥሎታል ። እንግዲያውስ አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ሁሉ ስለሚድን መዓት ፣ መቅሠፍት ከመግባቱ በፊት ለጸሎት ዝግጁ እንሁን (የሐ/ ሥራ ፪ ፡ ፳፩) ።

ጸሎት የሁሉ መክፈቻ ሲሆን የሰው ልጅ በራሱ ሥራ የምሕረቱን በር ዘግቶ ይገኛል ። ጸሎት ከፈጣሪ ጋራ መነጋገር ሲሆን በጸሎት ከረቂቁ ፈጣሪ ጋራ የሚነጋገሩና ስሜታቸውን የሚያረኩ ጥቂቶች ናቸው ፤ ጸሎት ሰው ከሌላው ፍጥረት ተለይቶ ወደ ፈጣሪው የሚቀርብበት ፣ ችግሩን የሚገልጽበት ፣ ይቅርታን የሚጠይቅበት መንገድነው ።

እንግዲያውስ ጸሎት ለሰው ልጅ ሁሉ የግድ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ማንኛውም



ሰው በማንኛውም ጊዜ መጸለይ አለበት ማለት ነው ። ጸሎት የዚህን ያህል አስፈላጊነቱ ግልጥ የሆነ ጠቃሚ መሣሪያ ስለ ሆነ የሰው ልጅ ሁሉ ለጸሎት ዝግጁ ሆኖ ሰው መሆኑን ሰውነቱን ዐውቆ ጥቅሙን እንዲያገኝ የጸሎቱን ሥነ ሥርዐት መጀመሪያ ማወቅ አለበት ። ስለዚህ በሚከተሉት ምዕራፎች አስረዳለሁ ።

ሊ/ ሥ/ ሀ/ ማ/ ወ/



www.ethiopianorthodox.org

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ። (፫ጊዜ እንበል) ማንኛቸውንም ሥራ ከመጀመራችን በፊት ጸሎት መጸለይ ተገቢያችን ነው ። ምክንያቱም ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋራ መነጋገር ማለት ነው ። ማንኛውም ሰው ከመኝታው ተነሥቶ መጀመሪያ የሚነጋገረው በአቅራቢያው ከሚኖሩ ከቤተ ዘመዱ ጋራ ነው ። ይህም ሊሆን የሚገባ ክብር ነው ፣ እንዲሁም ከሆነ አንድ አማኒ በመጀመሪያ ከመኝታው እንደ ተነሣ በቅርቡ ከሚገኝ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር መወያየት አለበት ማለት ነው ። ስለዚህ ከመኝታችን ስንነሣ ጸሎት ልመና ወደ ፈጣሪያችን እናቀርባለን ፣ ምኞታችንን እንገልጣለን ። ጸሎትም ደግሞ



ከማድረጋችን በፊት ገጻችንን እናማትባለን (በፊታችን ላይ የመስቀልን ምልክት እናደርጋለን) ። ገጻችንንም ስናማትብ እጣቶቻችንን አመሳቅለን ከግንባራችን ወደ ደረታችን ከግራችን ወደ ቀኛችን ጣቶቻችንን የመስቀልን ምልክት እናደርጋለን ። የመስቀልን ምልክት በማድረግ ባማተብን ጊዜ ፣ የተሰቀለውን ክርስቶስንና የተሰቀለበትን ክቡር መስቀሉን ማስወታስ ይሆንልናል ። ደግሞም በዚህ በጣቶቻችን ምልክትነት ያማተብን እንደሆነ ጠላታችንን ድል እንነሣበታለን ። « ለእመ ኮንኩ አው ፅእ አጋንንተ በአጽባዕተ እግዚአብሔር (ሉቃ/ ፲፩ ፡ ፳) ይላልና ፣ እንዲሁም ፫ቱን ዕጣቶች በማገናኘት፣ ወይም የመስቀልን ምልክት በማድረግም እናማትባለን ፣ ፫ቱን አንድ ማድረጋችን ሥላሴ አንድ ሲሆኑ ሦስት ፣ ሦስት ሲሆኑ አንድ የመሆን አምሳል ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከራሳችን መጀመራችን እግዚአብሔር አብ ምንም በዓለም ምሉእ ቢሆን ስለልዕልናው በከፍተኛ በልዑልነት በሰማይ መኖሩን ያመለክታል ። ወደ ደረታችን ማውረዳችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከከፍተኛ ዙፋኑ ወደ ምድር ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማኅፀን የማደሩና ሰው የመሆኑ ምሳሌ ነው ። ከግራ ወደ ቀኝ ማማተባችን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሰውን ከኀጢአት ወደ ጽድቅ ፥ ከክፋት ወደ በጎነት እንደሚመልስ ለማስረዳት ነው ። እንዲሁም ክርስቶስን አይሁድ መስቀሉን አሸክመው ያመላለሱትን ፥ ያሠቃዩትን ያስተምረናል ። እንዲሁም የክርስቶስ የመከራውና የሥቃዩም ተሳታፊዎች እንደ ሆን ያጠይቃል ። ይህን ሦስት ጊዜ መላልሰን እናደርጋለን ፤ ምክንያቱም ሥላሴ ምንም በባሕርይ ፥ በአምላክነት አንድ ቢሆኑ



በአካል ፥ በስም ፥ በግብር ሦስት የመሆናቸው ምሳሌ ነው ፤ ቃሉ ፫ ጊዜም ሲመላለስ አለመለዋወጡ አንድ መሆኑ ሥላሴ ምንም በስም ፥ በግብር ፫ ቢሆኑ ፥ በባሕርይ በመለኮት አንድነታቸውን ፤ ትክክለኝነታቸውን ይገልጣል ፥ ( ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፬) ይኸን የመሰለ ትችትና ምስጢር ስላለው ፤ ማንኛውም ሰው በዚህ መልክ ሊፈጽመው ይገባዋል ። በዚህ መልክ የጸሎቱን ሥነ ሥርዐት ማከናወን ለሰው ልጅ ሁሉ በተለይም ለክርስቲያኖች ሁሉ ተገቢ ነው ።

## ምዕራፍ ፪ ፤ የጸሎት አስፈላጊነት ።

የሰው ወገን ሁሉ ከየት እንደ መጣ ማወቅ ፥ ማን እንደ ፈጠረው ለይቶ ማመን ፥ የፈጣሪውንም ውለታ ለይቶ ማወቅና ማመስገን ለማንኛውም ሰው የግዴታ ተግባሩ ነው ። እምነት ማለት የማይታይ አምላክ በርግጥ እንዳለና ይህን ዓለም አከናውኖ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

የፈጠረ እርሱ እንደሆነ እርሱም ራሱ ሰው
ዬው ከፍጥረቱ ልዩ ኛው መሆኑን በፍጹም ልቡና
ማመን (ማወቅ) ነው ። እምነት ከፈጣሪ
ጋራ እንደመተያየት ይቈጠራል ። ጸሎት ፥
ደግሞ የዚህን ቅዱስ አምላክ ቸርነቱን ፤ ታጋ
ሽነቱንና ቅዱስነቱን እየገለጡ ማመስገን ፥
ለራስም ጤንነትን ፥ ሰላምን መለመን ነው ።
ይህም ከእግዚአብሔር ጋራ እንደ መነጋገር
ይቈጠራል ። እንግዲያውስ ማንም ሰው ከሰው
ጋራ ከመነጋገሩ በፊት ፤ ከእግዚአብሔር
ጋራ መነጋገር ፥ ሰውን ደጅ ከመጥናት ይልቅ
እግዚአብሔርን ደጅ መጥናት ይበልጠዋል።
ስለዚህ ጧት ከመኝታው ሲነሣ ፥ በምግብ
ጊዜ ፥ ማታም ወደመኝታው ሲሄድ ፥ እን
ዲሁም በልዩ ልዩ አጋጣሚ ጊዜ ፤ ለምሳሌ ፥
በተደሰተ ጊዜ መዘመር ፥ በተቸገረ ጊዜ
መለመን በየጊዜው በቀጥታ ከፈጣሪው ጋራ
መተያየት ፥ መነጋገር አለበት ። ሲጸልይም



የሚለምነውን እንደሚያገኝ በፍጹም ልቡ
ናው አምኖ ከፈጣሪው ጋራ በልቡ ተገና
ኝቶ ተጣብቆ መጸለይ አለበት ። እምነት
ያለ ጸሎት ፤ ጸሎትም ያለ እምነት አንዳች
ግዳጅ አይፈጽምም ። ስለዚህ ሳያምኑ መጸ
ለይ ፥ ኪሴ የሌለውን ሰው እንደ መለመን
ይቈጠራል ። እግዚአብሔርን ደግሞ እያመኑ
እንዲሁ ይቅርታ ካልጠየቁ ፥ ጸሎት ካልጸ
ለዩ ፤ አንድ ሰው ችግር ጸንቶበት ረዳት
ሞልቶት ችግሩን እንደማይገልጥ ፥ ርዳ
ታም እንደማይጠይቅ ይቈጠራል ። ስለዚህ
ፈጣሪያችን ቸር ሰውን ወዳድ እንደ ሆነ እን
መን ። ካመነውም ዘንድ እናመስግነው ።
ጸሎት እንጸልይ ፥ ማለት በሃይማኖታችን እን
የው ፤ በጸሎታችን እንነጋገረው ፤ ግዳጃችንና
ብሶታችንን ገልጠን እንንገረው ፡ ቸርነቱን ፥
ምሕረቱንም እየመሰከርን እናመስግነው ።

www.ethiopianorthodox.org

በአለፈው ምዕራፍ ጸሎት መጸለይ እንዲገባ በተለይ በጧትና በማታ መጸለይ እንዲገባ ተናግረናል ። የጸሎቱ ጊዜ ይኸ ብቻ አይደለም ፤ ወይም ሊሆን አይገባም ፤ ምክንያቱም ጸሎት ሲጸልዩ ሰዓት ጊዜ ሳይወስኑ ሳያቋርጡ መጸለይ ይገባልና ። ሳያቋርጡ መጸለይ እንዲገባ ቅዱስ ጳውሎስ (፩ኛ ተሰሎ/፭ ፡ ፲፯ ፤ ሉቃ/፲፰፡፲)፤ ጸልዩ ሳትታክቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ በሥራው ሁሉ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና በክርስቶስ ኢየሱስ ፤ ጸሎት መጸለይ ከእግዚአብሔር መነጋገር ፡ ሙወያየት ፥ ወይም የሚሹትን ነገር ከእግዚአብሔር መለመን ስለ ሆነ፥ ለዚህ ቅዱስ ተግባር ጊዜ ሊመረጥለት፥ ሰዓት ሊወሰንለት አይገባም ፤ በማንኛው ዕለት ፡ በማንኛውም ሰዓት መጸለይ



እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ ቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው ያስረዳናል ። « በዕለት ኅሪት እሰምዐከ፤ወበዕለተ መድኃኒት አድኅንከ፤ የምኬ ዕለት ኅሪት ወዮምኬ ዕለተ አድኅኖ » (ኢሳይ/ ፵፱፡፰ ፤ ፪ኛ ቆሮ/ ፮ ፡ ፪) ትርጓሜውም በተመረጠችዪቱ ዕለት እሰማሃለሁ። በምረዳበት ቀንም እረዳሃለሁ ፤ የተመረጠቺይቱ ዕለት ዛሬ ናት፤የመድኀኒትም ዕለት ዛሬ ናት ማለት ነው፡፡

ይህም ማለት ቀኑ ሁሉ ዛሬ ይባላልና የተመረጠችይቱ ቀን ዛሬ ናት ፤ የመድኀኒትም ቀን ዛሬ ናት ማለቱ ሁል ጊዜ ለጸሎት እንድንተጋ፥እንድንነቃ የሚያመለክተን ነው ።

ጸሎትም ስንጸልይ ኪቶ መሰልቸት የለብንም፤መልሰን መላልሰን ግዳጃችን እስኪፈጸም፤ ከተፈጸመም በኋላ አብዝተን ፤ መላልሰን መጸለይ አለብን ፤ ምክንያቱም ማንኛውም ሰው አብዝቶ ኪሠራ ዘንድ መልካም ውጤትን እንደሚያገኝ ክርስቶስ በጨካኙ መኰንንና በድሃዪቱ ሴት መስሎ ተናግሮአል ።

www.ethiopianorthodox.org

(ሉቃ/ ፲፰፥፩—፲ ) ፤ ይህንም እውነተኛ ትምህርት ቅዱስ ጳውሎስ ተከትሎ « ጸሎትን የምታዘወትሩ ሁኑ ፤ ለርስዋም ስታመሰግኑ ትጉ » ( ቆላስ. ፬፥፪ ፤ ሮሜ ፲፪ ፡ ፲፪ ፤ ፊልጵ. ፬ ፡ ፮ ) እያለ ያስተምረናል ። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ይህንኑ አጽድቀውታል ። ጸሎት መጸለይ ቢገባና በማንኛውም ሰዓት መጸለይ ቢቻል ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የሕዝብዋ የድካም ተካፋይ እንደመሆንዋ መጠን ፤ ክርስቶስም መከራ የተቀበለባቸውን ፤ እኛን ለማዳን ሥራ የሠራባቸውን ጊዜ በማስታወስና በመምረጥ የተለዩ ሰዓቶች ለጸሎት ወስናለች ። ይኸውም ፤

<u>፩ኛ ፤ የጧት ጸሎት</u> ፡ በጧት ከመኝታ ሲነሡ ፊትን ታጥቦ ወዲያው በቀጥታ ከፈጣሪ ጋራ መነጋገር ፤ (መጸለይ) ይገባል ። ከፍ ያለ ዋጋንም ያስጣል ። በጧት መጸለይ ከባዱን ጨለማ አሳልፎ ተስማሚውን ብርሃን ለሰጠ ፤ ደግሞም የበላነው ከብዶን የጠጣነው አንዝዞን ሳንሞት ፤ በሰላም ስላሳደረን ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ፤ እንዲሁም በሰላም እንዳሳደረን በሰላም እንዲያውለን መለመን ይገባናል ፤ የለመኑትን የማይነሣ ፤ የነገሩትን የማይረሳ እግዚአብሔር እንደለመኑት ይፈጽማልና ።



<u>፪ኛ፤ የሦስት ሰዓት ጸሎት ፤</u> በ፫ ሰዓት መጸለይ ይገባል ። ይህችም ሰዓት መድኀኒታችን ክርስቶስ በዕለተ ዐርብ ለእኛ ካሣ ለመሆን በጲላጦስ ዐደባባይ ይሰቀል ዘንድ የተፈረደበት ሰዓት ናት ። ስለዚህ መድኀኒቴ ክርስቶስ ሆይ ለኔ ስትል መከራ መስቀልን ተቀበልክ ፤ እንደ ወንበዴ ይሙት በቃ ተፈረደብህ ። እንደ ኀጢአተኛ ሞትህ በመስቀል እንዲሆን አደረጉ እያሉ የሰውን ጨካኝነት ፤ የርሱን ትዕግሥትና ሥቃይ

ማሰብ መጸለይ ይገባል ። ደግሞም ቀድሞ በኔ ኀጢአት ገብተህ ኀጢአተኛ ተባልክ ፤ ሳታጠፋ በደለኛ ተባልክ ፤ ለኔም ስትል ሞትክ ፤ ለኔ ስትል የሞትህ ከዛሬው በደሌ አድነኝ ፤ ክብርህን ፤ ጸጋህን ዐድለኝ እያሉ መጸለይ ፥ ይገባል ።

፫ኛ/ የ፮ ሰዓት ጸሎት ፤ በ፮ ሰዓት መጸለይ ይገባል ። ይኸውም መድኀኒታችን ክርስቶስ ስለኛ የተሰቀለበት ሰዓት ስለሆነ መድኀኒቴ ክርስቶስ ሆይ ለኔ ስትል ሳታጠፋ እንደ አጥፊ ተቈጠርክ ፤ ሳትበድል እንደ በደለኛ ተሰቀልክ እያሉ መከራ መስቀሉን ማሰብ ፥ ለራስም ደግሞ የኀጢአት ሥርየትን መለመን ቸርነቱንም ገልጦ መናገር ይገባል ።

፬ኛ፤ የ፱ ሰዓት ጸሎት ፤ በ፱ ሰዓት መጸለይ ይገባል ፤ በዚህች ሰዓትም ደግሞ በሰው በደል



የገባው ክርስቶስ ቅድስት ነፍሱን በሥልጣኑ ከቅዱስ ሥጋው የለየበት (የሞተበት) ሰዓት ስለ ሆነ ፥ ሞት የማይገባህ ክርስቶስ ለኔ ስትል መራራ ሞትን ቀመስክ እያሉ መከራውን ማስታወስና ማመስገን፥ለራስም ደግሞ መጸለይ ከሞተ ሥጋ ከሞተ ነፍስ እንዲያድነው መለመን ይገባል ፥

፭ኛ፤ የማታ ጸሎት ፤ የማታ ጸሎት ማድረግ ይገባል ። ይህም መድኀኒታችን ክርስቶስ ወደ መቃብር የገባበት ሰዓት ነው ። ስለዚህ ሰማይና ምድር የማይወስንህ አምላክ ለኔ ስትል በሦስት ክንድ ከስንዝር መቃብር ተወሰንክ ፥ ተቀበርክ እያሉ አምላክ ሲሆን ወደ መቃብር መውረዱን ማሰብ ለራስም ሙስና መቃብር አታሳየኝ እያሉ መለመን ይገባል ። ቀጥሎም ለቤቱ ስፋት ፥ ለሀብቱ ድርጅት ሲወጣ ሲወርድ ውሎ በሰላም ከቤቱ ስለ ገባና ቤቱ

www.ethiopianorthodox.org

ንም በደኅና ስላገኘው ማንኛውም ሰው ፈጣሪውን ማመስገን ይገባዋል ።

<u>፯ኛ፤ ጸሎተ ንዋም ፤</u> በምኝታ ጊዜ መጸለይ ይገባል ፤ በዚህም ሰዓት ሰው ሁሉ ሲወጣ ሲወርድ ውሎ ከድካሙ የሚያርፍበት ፣ የደከመበትን በሰላም በልቶ ጠጥቶ የሚተኛበት ጊዜ ስለ ሆነ፣ በሰላም ያዋልከኝ አምላኬ አመሰግንሃለሁ ፤ እንዲሁም በሰላም እንድታሳድረኝ እለምንሃለሁ እያሉ መጸለይ ይገባል ።

<u>፰ኛ፤ የሌሊት ጸሎት ፤</u> በመንፈቀ ሌሊት ማመስገን ይገባል ። በዚህችም ሰዓት መድኀኒታችን ክርስቶስ በተቀበረ በሦስተኛው ቀን መቃብር ከፈቱልኝ ፣ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ብድግ ብሎ ተነሥቶ አቸናፊነቱን የገለጠባት፣ደስታውን የሰበከባት ሰዓት ናት።ስለ አቸናፊነቱ ምስጋናን ማቅረብ እንዲሁም ለራሴ የክብር ትንሣኤን እነሣ ዘንድ ዐድለኝ እያሉ መለመን ነው ፤ በሌሊት መጸለይ እንደሚገባ ቅዱሳት መጻሕፍት ተስማምተውበታል ። ነቢዩ ዳዊት «በሌሊት መካከል እነሣለሁ ስለ እውነተኛ ፍርድህም አመሰግንሃለሁ ። ( መዝሙር ፻፴፬ ፡ ፩—፪) ክርስቶስም ሌሊት ወይም ቀን እመጣ አታውቁምና ተግታችሁ ነቅታችሁ ኑሩ ጸልዩ ሲል ያስተምረናል ( ማቴ/ ፳፬ ፡ ፵፪ ) እንዲሁም በጌቴሴማኒ ሌሊት እየመላለሰ ሦስት ጊዜ ከጸለየ በኋላ ተማሪዎቹን እንዲህ ሲል አዘዛቸው« ጸልዩ ትጉም ወደ መከራ እንዳትገቡ ፣ ነፍስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነውና (ማቴ/፳፮፡ ፴፮—፵፩) ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስም በእስር ቤት ሳሉ በመንፈቀ ሌሊት ተነሥተው ሲጸልዩ ፣ እግዚአብሔርንም ሲያመሰግኑ መሬት ተናወጠች ፤ እግር ብረቱ ወለቀ ፤ እነርሱም ከመከራ ዳኑ። (የሐዋ/ ሥራ ፲፮፡ ፳፭) ስለዚህ ሰው የሆነ ሁሉ ምንም በሥጋዊ ሐሳብ የተዋጠ ሁኖ ለዚህ ቅዱስ ተግባር ምቹ ጊዜ ቢያጣለት ጸሎት



www.ethiopianorthodox.org

መጸለይ ፥ እግዚአቤሔርን ማመስገን ግዴታ መሆኑን ዐውቆ ይህን ቅዱስ ተግባር በተመቸው ጊዜ መፈጸም አለበት ፤ የቤተ ክርስቲ ናችንም ሕግ ነው ። ( ፍትሐ ነገ/ አንቀጽ ፲፬) ከሃይማኖታችን ውጭ የሆኑ ብዙዎች ሲፈ ጽሙት ይገኛሉ ፤ እንኳን ተራው ሕዝብ በሰ ልፍ ያለ ወታደርም ቢሆን ይፈጽመዋል ፤ እኛ በበለጠ ይኽን አክብረን መያዝ አለብን ።

## ምዕራፍ ፬፤ ወዴት መጸለይ እንደሚገባ ፤

እግዚአብሔር በዓለሙ ሁሉ ምሉ ነው ። ስለዚህም ፍጥረቱ ሁሉ በያለበት ቦታ ፥ በየግ ዕዛኑ ፥ በየመጠኑ ፥በየችሎታው ያመሰግነዋል። እንደዚህም ሁሉ ሰውም በያለበት በየተመ ቸው ቦታ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገ ባል ። ስለዚህ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ያስ ረዳናል ። «ምድር ለእግዚአብሔር ናት፤ ምላት ዋም ሁሉ ፤ በርስዋ የሚኖሩም ሁሉ» መዝ/



፳፬ ፥ ፩ ) ከሁሉ በፊት ግን ጸሎትን በ፫ እንከ ፍላለን ፤ እነዚህም ፤ ፩ኛ. የብቻ ጸሎት ፥ ፪ኛ- የቤተ ሰብ ጸሎት ፥ ፫ኛ የማኅበር ጸሎት ናቸው ።

፩ኛ የብቻ ጸሎት ፤ ከዚህ በላይ የዘረዘርነው ለብቻም ሆነ ወይም በማኅበር በተመቸው ቦታ መጸለይ እንዲገባ የሚያስተምረን ነው። ብዙ ጊዜ የብቻ ጸሎት የሚባለው በተመቸው ቦታ ሊያደርጉት የሚገባ ነው ፤ በተለይ ግን ባሕ ታዊ (መነኰሴ) ሁኖ በበረሀ በምድረ በዳ ስለሚኖር፤ ወይም እስረኛ ፥ ግዞተኛ ሰወ ሁኖ እንደ ልቡ ለመውጣት ፥ ለመግባት ፈቃድ የሌ ለው ይሆንና በተመቸው ሰዓት ባለበት ሁኖ መጸለይ ይችላል ። ዮናስ የአምላክ እስረኛ ሆኖ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሁኖ ይጸልይ ነበር፤ ስለዚህም ወሃውም ሆነ ዓሣነባሪው ጉዳት አላመጡበትም ። (ዮናስ ምዕ/፩፥ ፪—፫) ዳንኤ ልም በእስር ቤት ሳለ ከአንበሳ ጋራ እየታ

www.ethiopianorthodox.org

ገለ ይጸልይ ነበር ። ስለዚህም አንበሶች አንዳች ጉዳት አላመጡበትም ፤ የጸሎቱ ኀይል ልሳናቸውን ዘጋው እንጂ ሠለስቱ ደቂቅም እንደዚሁ በሚቃጠል እሳት ውስጥ ታስረው ሳለ ጸሎታቸውን አላቋረጡም ፤ የለመኑትን የማይነሣ ፥ የነገሩትን የማይረሳ እውነተኛው አምላክ ደግሞ ጸሎታቸውን ሰምቶ ሰዎቹን ከነደደ እሳት አዳናቸው ። የልብሳቸውም ቀለም እንኳ አንዱ አልተለወጠም ፤ (ዳንኤል ፫፡፳፪—፴) ነገር ግን እነርሱን ለጥፋት ይመኙ የነበሩትን የባቢሎንን ሰዎች አቃጠላቸው ። ጳውሎስና ሲላስም እንዲሁ በእስር ቤት ሁነው በመንፈቀ ሌሊት ይጸልዩ ነበር ፤ የሚለምኑት አምላክ እንቅልፍ የሌለው ሌት ከቀን የሚረዳ ስለሆነ ፥ መላኩን ልኮ እነርሱንም ሌሎችንም እስረኞች አዳነ ። (የሐዋ/ ሥራ ፲፮ ፥ ፳፭)



ስለዚህ ማንኛውም ሰው በችግርም ሆነ በምቾት ፥ በመታሰርና በምርኮ ፥ በደስታም ላይ ፥ በጫጉላ ላይም ሳለ ቢሆን እግዚአብሔርን ከማመስገን ወደኋላ ማለት የለበትም ። በደስታ ሳሉ ቢጸልዩና እግዚአብሔርን ቢያመሰግኑ ደስታቸውን ፍጹም አድርጎላቸው ሁል ጊዜ ሲደሰቱ ይኖራሉ ። በመከራ ሳሉ ቢጸልዩና አውጣን እያሉ ቢለምኑት ከመከራ ያወጣቸዋል ። « ያዘነ ይጸልይ ፥ የተደሰተ ቢኖር ይዘምር» (ያዕ. ፭፡፲፫) ፤ አንዳንድ ሰዎች ግን መከራ ሲያገኛቸው እግዚአብሔርን የጐዳን እየመሰላቸው ከጸሎት ፥ ከአምልኮት ፥ ከበጎ አድራጎት ርቀው እንዲሁ በኀይላቸው የበለጸጉ ፥ በጥበባቸው የዳኑ እየመሰላቸው ከዚህ ቅዱስ ተግባር ርቀው ይገኛሉ ። እውነተኛው ክርስቲያን ግን መከራም ደስታም ሳይለውጠው ሁል ጊዜ ፈጣሪውን በማገልገል ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ኛ. የቤተ ሰብ ጸሎት ፤ ደግሞ በጧት
በማታ በምግብ ጊዜ ወይም ቤተ ሰቦቹ
አክትተው በሚሰበሰቡበትና በሚገናኙበት
ጊዜ አንድ የጸሎት ቦታ ወስነው ወይም
ከተመቻቸው ቦታ ላይ ሁነው መጸለይ አለ
ባቸው ። የቤተ ሰብ ጸሎት እንደሚገባ ኖኅ
ቤተ ዘመዶቹን ይዞ ይጸልይ ነበር ፤ ስለዚ
ህም ዓለም በሞላው በንፍር ውሃ ተቀቅሎ
ሲጠፋ የቤተ ሰብ ጸሎት የሚያደርግ ኖኅ
ስምንት ራሱን ብቻ ዳነ ። (ዘፍ. ፲፥፳—፳፪)
ኢዮብም እንዲሁ በጧት በማታ ልጆቹን
እየጠራ ወደ ፈጣሪያቸው እንዲለምኑ
ያዛቸው ፥ ጸሎትም ያስተምራቸው ነበር ፤
(ኢዮብ ፩፥፫—፮) ይህ ቅዱስ ተግባር ወላድ
ለሆኑትና ብዙ ቤተ ሰብ ላላቸው ሁሉ እንደ
ሚገባ ማወቅ አለባቸው ። ብዙ ሰዎች ልጅ
አጣን በማለት ፈጣሪያቸውን ሲያማርሩ ሲያ
ኮርፉ ይገኛሉ ፤ ለዚህም ሲሉ ወደ አባይ



ጠንቋይ ሲሄዱ ሥር ሲምሱ ፥ ቅጠል ሲበ
ጥሱ ጣዖት ሲያመልኩ ይገኛሉ ። ይህም
ከሆነ ወልዶ በደንብ ካለማሳደግ በጸሎት
በልመና እግዚአብሔርን የማይገናኝ ፤ ደስታ
ውን የማያካፍል ከሆነ አለመውለድ ይሻ
ላል ። መንፈሳዊ ስሜት ፤ ግብረ ገብነት በል
ጅነቱ ካልተዋሐደው ሌላ ትምህርት እናስ
ተምራለን ሲሉ መርዝ እንደ ማብላት መር
ዝም እንደ ማጠጣት ይቈጠራልና ፥ ወላድ ሁሉ
ከሁሉ በፊት ለልጆች ጸሎትና ምስጋና ደግ
ሥራሁሉ ማስተማር አለባቸው ፤ ከነርሱ
በላይ ሌላ ታላቅ አስተዳዳሪ እግዚአብ
እንዳለ ያስተማሩ እንደ ሆነ፥ በእግዚአብሔር
ሔርና በትልልቆች ሰዎች ላይ አክብሮትና
ፍርሃት ያድርበታል ። እንዲህም ከሆነ በማ
ፈር ከወንጀል ይድናል ፤ እነርሱን ያከብ
ራል ፤ ምክራቸውን ይቀበላል ። እንዲሁ በስድ
ያደገ እንደ ሆነ ግን እንደ እንስሳ ሁኖ የእንስ

ሳን ተግባር በመፈጸም ከሰው ተራ ወጥቶ
ይኖራል ፤ ይኸ ሁሉ የቤተ ሰብ ኀላፊነትን
ስለሚጠይቅ ለልጆች ለአሽከሮች ለገረዶች
በጠቅላላውም ለቤተ ሰቦች ጸሎትን ማስተማ
ርና አብሮ መጸለይ ይገባል ። ለምሳሌ ማዕደ
ቀርቦ እንጀራውን ሲቈርሰው «በስመ አብ
ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ሳይል የቈረሰው
እንደሆን ፩ኛ/ በረከት የለውም ፤ ፪ኛ/ በጎ
ይሉ ያገኘው እንጂ እግዚአብሔር የሰጠው
አይመስለውምና ፤ ስለዚህ ምግብ ሲጀመር
ምግቡን በዝናም አብቅለህ ፥ በፀሐይ አብስ
ለህ አዘጋጅተህ የሰጠኸኝ አምላክ ክብር
ምስጋና ይድረስህ ፤ አሁንም ይህ ማዕድ ለሥ
ጋዬ ፤ ለነፍሴ ኀይልን ፥ ጤንነትን የሚሰጥ
አድርግልኝ ብሎ መመገብ ያስፈልገዋል ።
ሲፈጽምም የተመገበው ከሰው ነቱ እንዲስግ
ማለት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለበት ።
ይህም ሲሆን የቤተ ሰብ ጸሎት በቤታቸ



ውና በሄዱበት፥በሚገኙበትም ቦታ መስሎ በታ
ቸው ሁሉ ሊያደርጉት ይችላሉ ።

የቀደሙ አባቶችና እናቶች የሥዕል ቤት
እያሉ የተለየ ቦታ ሰጥተው የተወሰኑ ካህናት
እየያዙ ይጸልዩ ቤተ ሰብንም ያስተምሩ ነበር፤
ይኸም ሊጠበቅና አሁንም ሊፈጸም ይገባ
ዋል ።

፫ኛ/ የማኅበር ጸሎት ፤ ደግሞ አንድ
እምነት ያለው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን፥
በአንዲት ሥርዐት የሚተዳደር ሕዝብ ሁሉ
የቤተ ክርስቲያን ኀላፊ በወሰነው ዕለትና፤
ቦታ ወይም ሰዓት ተሰብስቦ በአንድነት የሚ
ጸልዩት ነው ። የማኅበር ጸሎት ሁል ጊዜ
ሊሆን የሚገባው በቤተ ክርስቲያን ነው ።
ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ለምሳሌ
እንደ መስቀል በዓል ፥ እንደ ጥምቀት ያለ
በዓል የሆነ እንደ ሆነ፥ የቤተ ክርስቲያኑ አስ
ተዳዳሪ በወሰነው ቦታ ሊሆን ይችላል ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህም ጊዜ አንደኛው አባል ከቶ ሊለይ ወይም ሊቀር አይገባውም ። ሐዋርያት እንኳ በጥንተ ስብከት የታወቀ ቦታ የደረጀ ቤተ ክርስቲያን ሳይኖራቸው በአንድ ቤት እየተሰበሰቡ የማኅበር ጸሎት ያደርጉ ፤ እግዚአብሔርን ያመስግኑ ፤ ቅዱስ ተግባርንም ይፈጽሙ ፤ ማዕድንም ይባርኩ እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል ። (የሐዋ ሥራ ፪፡፵፪—፵፯) ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በሕሊናው ተገድዶ የማኅበር ጸሎትን በቤተ ክርስቲያን ያደርጋል ፤ ስለ ዚህ በየሳምንቱ እሑድ እሑድ በክርስቲያናዊ ትምህርት ምእመናን የሆኑ ሁሉ በኅብረት ምስጢራትን ሲካፈሉ ፤ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ፤ ክርስቲያናዊ ተግባራቸውን ሲፈጽሙ ይኖሩ ነበር ፤ ይኸም ሥርዐትም ከዕብራውያን የተወረሰ ነው ፤ ክርስቶስም ወደ ዚህ ዓለም ሲመጣ ይኸን ቅዱስ ሥርዐት



ሊያፈርስ ስላልወደደ በ፲፪ ዓመቱ ሊጸልይ ከሕዝቡ ጋራ ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ገባ እናገኘዋለን( ሉቃስ ፳፬፡፶፪-፶፫) በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው በማኅበር የሚጸልዩት ወይም በአንድ በተወሰነ ቦታ ሆነው እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው የሚጸልዩት ጸሎት ታላቅ ጥቅም አለው ። ምክንያቱም የማኅበር ጸሎት እንደሚጠቅም ቅዱስ እግዚአብሔር« ደግሞ እላችኋለሁ ከላ ንት ሁለቱ በምድር አንደ ቢሆኑ በልመና ቸው የለመኑት ሁሉ ይሆንላቸዋል ። ከሰ ማዩ ከአባቴ ዘንድ ሁለት ሁነው ወይም ሦስት ሆነው በስሜ ወደ ተከማቹበት እዚያ በመካ ከላቸው እሆናለሁና » (ማቴ/ ፲፰፡፲፱—፳) ። ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ማኅበር ጸሎት በሰፊው ያትታል ።

አሁንም ቢሆን በሽተኛ ካልሆነና የተለይ ችግር ካልገጠመው በቀር በማኅበር ጸሎት ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

የሚለይ ክርስቲያን ክርስቲያን ሊባል አይገባውም ። ራሱ ከአባልነት የተለየና ከጸጋው ከቸርነቱ የራቀ ነው ።

## ምዕራፍ ፫ ለባልንጀራ መጸለይ እንደሚገባ

በክርስቲያን ሃይማኖታችን በተለይም ኦርቶዶክሳዊ ትምህርታችን አንዱ እንደራሱ አድርጎ ላንዱ መጸለይ ፥ መለመን መሥራት እንደሚገባ ያስተምረናል ፤ ማለት ሁላችን ያንድ የክርስቶስ ልጆች የአንድ የክርስቶስ ቤተ ሰቦች ፥ የክርስቶስ አካሎች ስለሆን አንዱ አካል ሲታመም መላ አካሉ ይታመማል ፤ አንዱም ሲደሰት ፩ኛው አብሮ ይደሰታልና። (፩ኛ/ ቆሮ/ ፲፪፡፳) ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን ሁሉ አንዱ አካል ደኅና ይውል ዘንድ አንዱ አካል ለሁሉ አካል መጸለይ ተገቢ ነው ።



በክርስቶስ ትምህርት ውስጥ ለባልንጀራውና ለወንድሙ የሚል እንጂ ለራሱ የሚል አይገኝም ። ለዚህም ክርስቶስ አንድ ላይ መጸለይ እንደሚገባ ሲያስተምር « አባታችን ሆይ » አለ እንጂ አባቴ ሆይ» አላለም። «የዕለት እንጀራችንን ስጠን» አለ ፥ እንጂ የዕለት እንጀራዬን ስጠኝ አላለም ፤ «በደላችንን ይቅር በለን» አለ እንጂ አበሳዬን በደሌን ይቅር በለኝ አላለም ። « ወደፈተናም አታግባን ከክፉ አድነን» አለ እንጂ ወደ ፈተና አታግባኝ ከክፉም አድነኝ አላለም።

ይህ ሁሉ የሚያስተምረን ለግላችን እንዳ ልተፈጠርን ለግላችንም ልንኖር የማንችል መሆናችንን የሚያስረዳና አንዱ ለአንዱ መጸለይ እንደሚገባ ነው ፤ እንኳን ለወዳጅ ለዘመድ ፤ ለጠላትም ሳይቀር መጸለይ እንዲገባ ፥ የሰው ልጅም ለዓለም ሰላም ሁል ጊዜ መጸለይ ቅዱስ ተግባሩ እንደ ሆነ ፥ ክርስቶስ በአ

www.ethiopianorthodox.org

ውነተኛ ትምህርቱን ገልጧል ፤ ( ማቴ. ፳፯፡ ፵፬—፵፰) ፤ ቀጥሎም ራሱ በመስቀል ላይ ሳለ ለጠላቶቹ ለአይሁድ « አባት ሆይ የሚሠሩት ባላወቁት ነውና ይቅር በላቸው » ሲል ወደ ባሕርይ አባቱ ለመነላቸው ። ይህንም ተከትሎ ቅዱስ እስጢፋኖስ ለሚደበድቡት ሰዎች ጸለየላቸው እንጂ ፥ አልጸለየባቸውም « ዕዳ በደል አታድርግባቸው ይህን የሚሠሩት ባላወቁት ነውና » (የሐዋ/ሥራ ፯፡ ፶፱—፷) ።

ክርስቲያን በማንኛውም ነገር ለግሉ ለራሱ የሚሠራው ነገር ከቶ የለውም ፤ ለባልንጀራው ፥ ለወገኑ ፥ ለሀገሩ እንጂ ፥ ክርስቲያን ሁሉ የክርስቶስ ተከታይ ስለ ሆነ፥እንደ ክርስቶስ መሆን ግድ አለበት።ክርስቶስ ለሰው ሠራ ፤ ለሰው ተላለፎ ሞተ ፤ እንግዲያስ ክርስቲያን ሁሉ ለሌላው መጸለይ አለበት ። እንኳንስ ለሕያዋን ወገኖቻችን በክርስቶስ አምነው ለሞቱት ክርስቲያኖች ሁሉ መድኀኒታችን



ክርስቶስ ይቅር እንዲላቸው መጸለይ እንዳለብን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ታስተምረናለች ። ይኸም ከሆነ ሁላችን በግልም በቤተ ሰብም በማኅበርም ጸሎታችን ለወገኖቻችን ፥ ለሀገራችን እንዲሁም ለዓለም በጠቅላላው መጸለይ አለብን ። ራሱን ወይ ለራሱ ብቻ ሊኖር የሚችል ከቶ የለም ፤ ሰው ለሰው መፈጠሩን እንወቅ እንግዲያስ ሰው ለሰው መጸለይ ግዴታው መሆኑን አጥብቀን እንረዳ ስለዚህም ለጸሎት ጽሙዳን እንሁን ።

## ምዕራፍ፮ ስንጸልይ እንዴት መሆን እንደሚገባን

ጸሎት መጸለይ ከፈጣሪ ጋራ መነጋገር ነው ብለን ተናግረናል ። ስለዚህ እንኳን ከእግዚአብሔር ከ፩ ትልቅ ሰው ፊት ስንደርስ ወይም ስንነጋገር ቁመን ቀጥ ብለን ስለ ሆነ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለጸሎት ስንዘጋጅ ቁመን ቀጥብለን ልቡናችንን ፣ ዓይናችንን ከክፉ ነገር ከልክለን ፣ እንገታችንን በትሕትና ዘንበል አድርገን ቀኝ ግራ ሳንመለከት መጸለይ አለብን ። እንዲሁም ደግሞ ቁመን ልንጸልይ እንችላለን ፤ ቁሞ መጸለይ እንደሚገባ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ያስተምረናል ፤ "ማለዳ ድምፄን ትሰማለህ ፤ አቤቱ ማለዳ እቆማለሁ ፤ ለአንተም እታያለሁ" (መዝ/ ፭ ፡ ፫) ይኸም የቤተ ክርስቲያናችን ሕግ ነው ፤ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፬)

ሦስተኛም ደግሞ እየሰገዱ እየተንበረከኩ መጸለይ ይቻላል፤ ይኸውም እንዲገባ ብዙ አስረጅ አለን ፤ ለምሳሌ መምህራችን ክርስቶስ በጌቴሴማኒ እየሰገደ ጸልዮአል (ማቴ/፳፮፡፴፱) የቤተ ክርስቲያናችንም ሕግ ነው ፤ (ፍት/ ነገ/ አንቀጽ ፲፬)። ምንም በማንኛውም ዐይነት ቢጸልዩ ማለት ቁሞም ሆነ ወይም ተንበርክኮ መጸ



ለይ ይቻላል፤ግን ሁልጊዜአንገቱን ወደመሬት ቀለስ ዘንበል ማድረግ አስፈላጊ ነው ። ይኸውም ትምህርት ፍርሀት መሆኑን የሚያስተምር ነው ። ለምሳሌ መጸብሐዊውን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ እንመልከት፤ ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ፤ ፩ኛው ፈሪሳዊ ነበር ፤ ፪ኛው ደግሞ መጸብሐዊ ፤ ፈሪሳዊው አንገቱን አቅንቶ ፣ ልቡን ዘርቶ በመጥፎ ሥራው ኮርቶ ሲጸልይ እግዚአብሔር ሳይሰማው ቀረ ። ነገር ግን መጸብሐዊው አንገቱን ቀለስ አድርጎ በትሕትና ቃል ፈጣሪውን ቢለምነውና ንስሓውን ቢናገር ከፈሪሳዊው ይልቅ እርሱ ክብሮ ገንኖ ወደ ቤቱ ገባ የሚል አስረጅ እናገኛለን ። (ሉቃ/ ፲፰፡ ፲፫)

ስለዚህ ሁል ጊዜ ጸሎት በጸለይን ጊዜ ያለፈውን ኀጢአት እያሰብን ፣ እየተንቀጠቀጥን

www.ethiopianorthodox.org

የለመን እንደ ሆነ ፈጣሪያችን ላለፈው ይቅር ይለናል ፤ ከሚመጣውም ይጠብቀናል ። እንደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሲጸልዩም ሲሰግዱም በጠቅላላውም መንፈሳዊ ነገር ሲፈ ጽሙ ገጽን ወደ ምሥራቅ መመለስ ተገቢ ነው ፤ ምክንያቱም ምንም እግዚአብሔር በ፯ቱ ማዕዘን ምሉ ቢሆን ፊትን ወደ ምሥ ራቅ መልሶ መጸለይ እንዲገባ ክርስቶስ የ፪ኛ ጊዜ ምጽአቱን የሚገልጠው በምሥራቅ ነውና ፤ (ማቴ. ፳፬ ፡ ፳፯—፴፩ ፤ ሉቃስ ፲፯፡ ፳፬) የቤተ ክርስቲያንም ሕግ ነው፤(ፍትሐ ነገ/ አንቀጽ ፲፬ ፤ መዝ. ፳፯ ---) እጅን ዘርግቶ ወይም በደረት ላይ አመሳቅሎ መጸለይ ይገ ባል ። እጅን በደረት ላይ ማመሳቀሉ ትምህ ርት መስቀልን ይገልጣል ። እጅን ዘርግቶ መጸለይ ደግሞ የልመና ምልክት ነው ። ማለት አንድ ሰው ሲለምን ለማሳዘን እጁን ዘርግቶ ነውና ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ተወዳጅ



የሆነ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን እንዲህ ሲል ይመክረዋል ። "እኔም እልሃለሁ ወን ዶች ይጸልዩ ዘንድ በየስፍራው ፤ ተየ ቀደሱም እጆችን ወደላይ ይዘረጉ ዘንድ ያለቁጣና ያለመጠራጠር" (፩ኛ ጢሞ/ ፪፡፰) የቤተ ክርስቲያንም ሕግ ነውና ። (ፍትሐ. ነገ/ አንቀጽ ፲፬ ) ከዚህም አስቀድሞ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ እያለ ይዘምራል ፤ "በመቅ ደስ እጆቻችሁን አንሡ እግዚአብሔርን አመስግኑት" (መዝ/ ፻፴፬፡ ፪) ይህ ከዚህ በላይ የዘረዘርነው ሁሉ ተስማሚ ሲሆን አንድ ሰው እንደ ፈለገው ሆኖ ሊጸልይ ይችላል ። ይህም ሊፈጸም የሚችለው ብዙ ጊዜ በብቻ ጸሎት ነው እንጂ፤የማኅበር ጸሎት በሆነ ጊዜ ግን አንድ ዐይነት አንድ መልክ መሆን አለበት እንጂ የተለያየ እንደሆን እኩሉ በውዳሴ ከንቱ እኩሉም በማሽሟጠጥ ዋጋቸውን ያጣሉ፤ ለተመልካችም ቅሬታን ያሳያሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሲጸልዩ ደግሞ በጣም መጮህ አይገባም፤ ለራሱ እንዲረዳ አድርጎ መጸለይ አለበት ። የማኅበር ጸሎት ግን የሆነ እንደ ሆነ ፥ በአንድ ድምፅ ሁሉም ጮኸው እንደሆን ወይም በመካከለኛው ድምፅ እንደሆነ እርሱም እን ደዚያው ሆኖ መጸለይ አለበት ። ጸሎት ደግሞ ከመጠን በላይ ማብዛት የሚገባ አይ ደለም በመጠኑ ልቡ፣ን ወስኖ የሚለምኑትን አምኖ የምንግዴ ሳይሆን መለመን ይገባል። ብዙ ሕዝቦች ልቦናቸውን እያባከኑ ጸሎት በማብዛታቸው የሚሰማን ይመስላቸዋል ። በርግጥ እነዚህ ሰዎች ዋጋቸውን አጡ ፤ በጸለያችሁ ጊዜ ነገር አታብዙ እንደ አሕ ዛብ በነገራቸው ብዛት የሚሰማን ይመስላቸ ዋልና። (ማቴ.፮፡፯ ፤ ኢሳ/፩፡፲፭፤ ማቴ.፳፫፡፲፬ ፤ ሲል ክርስቶስ ይመክረናል ።



## ምዕራፍ ፯ የጸሎቱ ዐይነት

ጸሎት እንደ ሰውዬው ስሜት እንደ ጊዜው አኳኋን ሊጸለይ ይችላል ። ማለት ሰውዬው ብዙ ትምህርት የሌለው ይሆንና በሚችለው ቋንቋ ፤ የሚያውቀውን ጸሎት ሊጸልይ ይች ላል ። እንዲሁም ከፍ ያለ ዕውቀት ኑሮት ድርሰት ደርሶ ተግሣጽ ጽፎ መዝሙር ዘምሮ ይህንም የመሰለ ልዩ ልዩ ጸሎት ሊጸልይ ይችላል « ወንድሞቼ እናንተ በተሰበሰባ ችሁ ጊዜ ለያንዳንዱ መዝሙር አለው ። ትምህርትም አለው ፤ መገለጥም አለው » ። (፩ኛ ቆሮ/፲፬ ፡ ፳፮ ) ፤ ሲል ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ጻፈ ። በብቻ ጸሎት ጊዜ የፈለገውን የጸሎት ዐይነት ልዩ ድርሰት ሊጸልይ ይች ላል ፤ ነገር ግን በማኅበር ጸሎት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የወሰነችውን ጸሎት ብቻ ሁሉ ተባብሮ መጸለይ ፥ ተባብሮ መዘመር ይገባል።

www.ethiopianorthodox.org

ማንኛውም ሰው የማኅበሩን የጸሎት ሥነ ሥርዐት ማጥናት አለበት ፤ ከዚህም ጋራ ሁሉ ሊጸልየው በማንኛውም ጊዜ ሊጸልዩት የሚገባ ጸሎት ክርስቶስ ያስተማረው አጭር ጸሎት «አባታችን ሆይ» የሚለውንና የዳዊት መዝሙር የቅድስት ማርያም ምስጋና ውዳሴንና ቅዳሴን መጸለይ ይገባል ፤ እንዲሁም ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የጸሎት መጽሐፍ ብላ ያወጣችውን መመልከት ያስፈልጋል ። ነገር ግን ሰው ሁሉ በመጠኑ በየችሎታው መጸለይ ይገባዋል ስንል የጸሎቱን ዐይነት መለየት አለብን ፤ የጸሎት ዐይነት ወይም ሥነ ሥርዐት በሦስት ይከፈላል ።

፩ኛ ምስጋና ይባላል ፤ ይኸውም አንድ ሰው ቢሾም ፣ ቢሸለም፣ ቢደሰትም ፣ ቢያዝንም፣ቢተክዝም የሆነውን ቢሆን ፈጣሪውን ማመስገን መቀደስ የግል ሥራው ግዴታውም ስለ ሆነ ፤ በማንኛውም ሰዓት ፈጣሪውን ማመስ



ገን አለበት ወይም ግዴታው ይሆናል ፤ ይኸም ነገር ተገቢ እንደ ሆነ ፣ ክርስቶስ እንዲህ ሲል አስተምሮአል ። አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣልን ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነ እንዲሁም በምድር ” (ማቴ•፮፥፱—፲) ። የእግዚአብሐር ስም ሁል ጊዜ ይቀደስ፤ሁል ጊዜ ይመስገን ።

፪ኛ ልመና ይባላል ፤ ይኸውም እርሱ አባታችን ስለ ሆነ ፣ የነገርነውን እንደሚሰማን የለመነውን እንደሚሰጠን አምኖ የወንድምንም የራስንም ችግር ገልጦ መለመን ነው ። ስለዚህም ክርስቶስ እንዲህ ሲል እንድንጸልይ አስተምሮናል “የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ ፤ በደላችንንም ይቅር በለን ፤ እኛ የበደለንን ይቅር እንደምንል ፤ ወደፈተናም አታግባን ፤ ከክፉ አድነን እንጂ፤ ”(ማቴ•፮፥፲፪—፲፫) ። አሁንም ሁልጊ ዜም ቢሆን በደላችንን ገልጠን እንለምነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፫ኛ ደግሞ እንዲሁ ምስጋና ይባገል ፤

ስለ ቸርነቱ ስለ ታጋሽነቱ የለመኑትን ስለ መስጠቱ ደግሞ ምስጋና ማቅረብ ፤ ይልቁንም ሰው የተፈጠረ ለምስጋና ስለ ሆነ ፥ እንዲህ እያሉ ማመስገን ይገባል ። "መንግሥት ያንተ ናትና ኀይልም ምስጋናም ፤ ለዘለዓለሙ አሜን" (ማቴ/፮ ፡ ፲፫) የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ አምላክ አሁንም ክብር ምስጋና ይግባው ።

## ምዕራፍ ፰ የጸሎት ጥቅሙ

የጸሎት ጥቅሙ ሁለት ዐይነት ነው ፤ ፩ኛ በዚህ ዓለም ሳለን ከሚገጥመን ችግርና ፈተና ለማለፍ ፥ ለመዳን ስንል እንጸልያለን ፤ ምክንያቱም ሰው ሁል ጊዜ መከራን የለበሰ መከራን የተጐናጸፈ በመሆኑና ሁል ጊዜ አሽክላው እንደተጠመደ፥ መሰ ፣ክሉ እንደ ተረበረበ ነው፤ ከዚህ



ሁሉ ለመዳን በእግዚአብሐር አምኖ እግዚአብሔርን ለምኖ ጸሎት ያደረገ እንደሆን ይድናል ። "የእግዚአብሐርን ስም የጠራ ይድናል(የሐዋ. ሥራ ፪፡፳፩) ። በኖኅ ዘመን ዓለም ሁሉ በፍል ውሃ ሲጠፋ በእግዚአብሔር ያመነ እግዚአብሔርን የለመነ ኖኅ ከነቤተ ሰቡ ዳነ ። (ዘፍ.ምዕ.፰፡፰—፱) ። እንኳን ራሱ አምኖ ለምኖ ከወገኖቹ ውስጥ ደግ ሰው በሀገሩ ቢጸልይለት ከዚህ ዓለም ችግርና መከራ ይድናል (ዘፍ.፲፰ ፡ ፳፫—፴፫) ። ኀጢአትም ቢሠራ እንዲሠረይለት ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ሲል ያስረዳል" ማንም ከናንተ ከመከራ ላይ ቢሆን ይጸልይ ፤ ደስ ቢለው ይዘምር ማንም ከናንተ ቢታመም በቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን ይጥራ ፤ ይጸልዩለትም ፤ ዘይትም ይቅቡት በጌታ ስም ፤ የሃይማኖት ጸሎት ድውይን ትፈውሳለች ጌታም ያስነሣዋል ፤" ኀጢአት ሠርቶ እንደሆን ትሠረይለታለች

www.ethiopianorthodox.org

ያዕ.፭ ፡ ፲፫—፲፰) ። ክርስቶስም ሐዋርያትን ሲያስተምር "ጸልዩ ትጉም ወደ መከራ እን ዳትገቡ - - - (ማቴ/፳፮፡፵፩) ፤ ቀጥሎም እንዲህ ይላል" ሹ ታገኛላችሁ ፤ ለምኑ ይሰጣችኋል ፤ (ማቴ/፯፡፯—፰)

ብዙዎች ቅዱሳን እያመኑ ሁሉም እግዚአ ሔርን ለመኑ ፤ እግዚአብሔርም የለመኑትን መስ ጠት ልማዱ ስለ ሆነ አምኖ ለምኖ የቀረበት ከቶ የለም ። ሁል ጊዜ አውጣኝ ቢሉት ያወጣል ። በሰላም ጊዜ ዝም ብሎ በመከራ ጊዜ ብቻ መለመን ተገቢ አይደለም ። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የለም ። የሚሉ እንኳን ይለምናሉ ፤ ግን ድንነት በእምነት ስለሆነ ፥ የሚድኑት ጥቂቶች ናቸው ። ለምሳሌ ፥ ቦል ኒይ የተባለ ፈላስፋ እግዚአብሔር የለም እያለ ሲያስተምር ቈይቶ አንድ ቀን በመር ከብ ተሳፍሮ ሲጓዝ ማዕበል ተነሣና ባሕ ሩን ሲገሥጽ የተሳፈረው ሁሉ ወደ አም ላኩ ሲጸልይ እርሱም እንዲሁ ተንበርክኮ



ይለምን ጀመር ፤ በዚህን ጊዜ ብዙዎች አብ ረውት ያሉ ቀድሞ የሚያውቁት ፤ "ምንድን ነው ይህ የምትሠራው ለማንስ ነው የምት ነግረው ሳታምን ፤ ቀድሞ እግዚአብሔር የለም ትል አልነበረም ? ብለው ጠየቁት" እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ ። "እግዚአብሔርን የለም የሚል ሰው ሁሉ ሲመቸው ነው እንጂ በችግር ጊዜ ነውን ? አሁንማ ሞት ጥርሱን አግጥጦ ፥ ዐይኑን አፍጥጦ ሲመጣ እኔ ዝም ብል ተፈጥሮዬ ይወቅሰኝ የለም ?" ሲል መለሰ ይባላል ። እግዚአብሔርን ማሰ ብና መለመን ከደኅናው ቀን ጀምሮ ነው ፤ በተያዙስ ጊዜ ማምለጥ የለም እንጂ ሁሉም ይለምናል። ፪ኛ ስለ፪ኛው ሕይወታችን እንጸል ያለን ፤ ቅዱሳን ለጊዜው በዚህ ዓለም ይሠቃዩ እንጂ ፥ በነፍሳቸው ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያገኙ ዘንድ ይጸልያሉ ፤ በርግጥም አምነው የለ መኑት አምላክ ከ፪ኛ ሞት ያድናቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ያስተምራል ፤ "መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን" (ማቴ/፮፡ ፲) ምድራዊ ሥራችን ለሰማያዊው ምሳሌ ነው ። ማለት ስንጸልይ በምድር የሚሰማን በምድርም የሚረዳን ከሆነ ለሰማያዊውማ እንደ ምን ከፍ አድርጎ ይረዳን ፤ ስለዚህ ሰማያዊ መንግሥቱን ያወርሰን ዘንድ ሁል ጊዜ ለጸሎት ፣ ለምስጋና ጽሙዳን እንሁን ።

## ማጠቃለያ

እግዚአብሐር በዓለም ሙሉ እንደ ሆነ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ እንዳለው ቸርና ለጋስም እንደሆነ ማመን ስለዚህም ማመስገን ለራስም መለመን መጸለይ ይገባል ። ሁሉንም የሚያደርገው በዓለም ሙሉ ከመሆኑና ሁሉንም ለማድረግ ችሎታ ከመኖሩ ከቸርነቱ፣ ከለጋስነቱ የተነሣ



እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር ሳይቀላቅሉ ማመን ይገባዋል ፤ ክርስቶስ ሲያስተምር«ስለዚህ እላችኋለሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እመኑ እንድታገኙ ይሆንላችኋልም(ማር/፲፩፡፳፬) ሲል አስረድቷል ። ስንጸልይ ደግሞ እርሱ እንዲሰማን እኛ ተገቢዎች ሁነን መሄድ አለብን፤ ማለት ከቂም ከበቀል ርቀን እኛ ይቅር እንዳልን እርሱም ይቅር እንደሚለን አምነን መጸለይ አለብን ። ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት አይሆንምና የወሰደውን መመለስ፣ የበደለውን መካስ መታረቅ የግድ ያስፈልጋል፤ያለዚያ ከቶ ይቅርታ ሊገኝ አይችልም ። ክርስቶስ ሲያስተምር «እናንተ ይቅር ብትሉ እኔም ይቅር እላችኋለሁ ፤ እናንተ ግን የበደላችሁን ይቅር ካላላችሁ እኔም እናንተን ይቅር አልላችሁም»(ማቴ/፮፡፲፬-፲፭፤ ማር/፲፩፡፳፭-፳፮ ፤ ማቴ/፭፡ ፳፫)ሲል ያስጠነቅቀናል።

ስለዚህ ገና ጸሎት ከመጀመራችን በፊት የበደለን እንዳለ ብናውቅ በመጀመሪያ ይቅርታን

www.ethiopianorthodox.org

መጠየቅ ተገቢያችን ነው ። ክርስቶስ ሲያስተምር «ቍርባንህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ ከዚያም ብታስብ ለወንድምህ አንዳች በላይህ እንዳለው ቍርባንህን ከዚያ በመሠዊያው ፊት ተወው አስቀድመህም ሂድ ከወንድምህ ጋራ ታረቅ ፤ ኋላም ተመልሰህ ቍርባንህን አቅርብ ከጠላትህ ፈጥነህ ተስማማ ከርሱ ጋራ - - - -» (ማቴ/ ፭ ፡ ፳፫- ፳፬) ሲል ያስረዳል ። እንግዲህ በልባችን ቂምን ፣ በቀልን ፣ ተንኰልን ፤ ይዘን የምንሠራው በጎ ሥራ ፣ የምንሰጠው ስጦታ፣ የምንጸልየው ጸሎት ከንቱ ነው ፤ ማለት እንደ እባብ በገዛ መርዙ እንደሚሞት በልባችን ክፉ ሐሳብ እንጠፋለን ማለት ነው ። ጸሎት ልትጸልይ በተነሣህ ጊዜ የበደለህን ሁሉ ይቅር በለው አንተም ከፈጣሪህ ይቅርታን ታገኝ ዘንድ ይላል። (ማቴ/ ፲፩፡፭)የቀረው ቀርቶ አንድ ሰው መንፈሱና ሥጋው እንኳን ሲጣሉበት ማለት ሐሳቡ አልሰበሰብለት መንፈሱ አልገዛለት ሲለው



መጀመሪያ መንፈሱንና ሥጋውን ለማስታረቅ ወድቆ ተነሥቶ ፈጣሪውን መለመን ይገባዋል ። ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈሱን የሚልክላቸው ለልቡናቸው ጸጥታ ለሥራቸው እርጋታ ላላቸው ነውና ። በተለይም በምዕራፍ ፭ እንደተናገርነው ከራስ ይልቅ ለሀገር ለወገን ለባልንጀራ መጸለይ ይገባል ። እንግዲያውስ በማንም ቂምን መያዝ አይገባም ፤ ለሁሉ ጸጋ ምሕረት እንዲያገኝ መለመን ይገባል እንጂ ። የምንጸልየው ጸሎት ሁሉ ዋጋ ያሰጥ ዘንድ፤ከልብ መጸለይ ይገባል። ማለት«አመንኩ በዘነበብኩ»እንዳለው ልቡን ከአፉ ፣ አፉን ከልቡ አንድ አድርጎ የሚናገረውን አምኖ፣የሚያምነውንም እንዲናገር ያስፈልጋል ። « አፍ ይለፈልፋል ፤ ልብ ግን ነገርን ያሰናዳል » እንደተባለው ሳይሆን ለራሱም ሆነ ለባልንጀራው የሚጸልየው እንዲሆንለት እንዲደረግለት ማመን ፤ ይህንም የሚያደርግ እግዚአብሔር እውነተኛ የባሕርይ አም

www.ethiopianorthodox.org

ላክ እንደሆነ ባሕርዩ ረቂቅ ፥ አኗኗሩ ምጡቅ ሁኖ በየትኛው ቋንቋ በየትኛውም ቦታ ሁነው ቢለምኑት የሚሰማና ለመስጠት የሚችል የለመኑትን የማይነሣ ፥ የነገሩትን የማይረሣ ፥ የታመነ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ማመን እንዲሁም ቢሰጥ ቢሰጥም የማያልቅበት ባለጸጋ የማይሰለች የማይመረር ለጋስ መሆኑን ዐውቆ በፍጹም ልቡ፣ውም አምኖ መለመን አለበት። ወደ ርሱ ለጸሎት ስንቀርብ እርሱንም በጸሎት ስንነጋገር ምን ያህል ክብር አለን?በእርግጥም እርሱ ታላቅ ከሁሉ በላይ ነው ፤ ግን አንተ ትንሽ ነህ አንተ ታላቅ ነህ ወይም አንተ ድሃ አንተ ግን ባለጸጋ ነህ አይልም። ስለዚህ ለኛ ትልቅ ኩራት ስለሆነ ፤ ከንጉሠ ነገሥቱ ከእግዚአብሐ ር ለመቅረብ ለመነጋገር ችሎታ ሳይኖረን እርሱ በቸርነቱ በምሕረቱ ለዚህ እንድንበቃ ስላደረገን ከፍ ያለ ምስጋናን ማቅረብ አለብን ፤ በፊቃደ ሥጋችን ተመርተን ከርሱ እየራቅን ፥ ሕጉን



እየተላነፍን ለቅጣት ዝግጁ መሆናችንን አምነን ራሳችንን መክሰስ መውቀስ ቀድሞ የሠራነውን በመናዘዝ ለወደፊት ግን ከዚህ ካለፈው ኀጢአት ለመራቅ ቊርጥ ሐሳብ ማድረጋችንን እየተናዘዝን እየተጸጸትን መናገር አለብን ። ራስን አዋርዶ ልቦናን ሰብሮ የሚጸልዩት ጸሎት የምሕረት አስመጭና ላኪ ነው፤ ይኸንም ነቢዩ ዳዊት « እኔ ዓመፃዬን ዐውቃለሁና ኀጢአቴም ሁል ጊዜ በፊቴ ነው፤ አንተን ብቻ በደልሁ፤በፊትህም ክፉ አደረግሁ ፤ » (መዝሙር ፶፩፡ ፫-፬) ክርስቶስም ራሱ ሲያስተምር ሳይታክቱ ሳይሰለቹ ሳይመረሩ መጸለይ እንዲገባ የመኰንኑን ጨካኝነትና የድኀየን ትጋት ምሳሌ አድርጎ አስተምሮአል ( ሉቃ. ፲፰፡፩- ፲፬) ።

አንዳንድ ሰዎች ፍጹም ስሜት ሳይኖራቸው በልማድ ብቻ ይጸልያሉ ፤ ምንም ነገር ሳያገኙ የቀሩ እንደ ሆነ ተስፋ ይቈርጣሉ፤ ግን እኛ ስንጸልይ ፩ኛ/እንደምናገኝ አምነን ልባችንን ከርሱ

www.ethiopianorthodox.org

ጋራ አገናኝተን መጸለይ አለብን ፪ኛ ፤ የለመነ
ውን ብናገኝም ብናጣም ጥቅማችንን ለማግኘት
ብቻ ብለን መጸለይ የለብንም ፤ ነገር ግን ፈጣሪ
ያችንን ማመስገን ግዴታ እንዳለብን እርሱ
የምንሻውን ዐውቆ ለመስጠት ዝግጁ እንደ ሆነ
አምነን ያለማቋረጥ መጸለይ ተገቢ ነው ። ከዚህ
በላይ የዘረዘርናቸውን በመገንዘብ የሚጸልይ
ሰው ሁል ጊዜ እርምጃው ከእግዚአብሔር ጋር
ሆኖለት ከክብር ወደ ክብር ሲራመድ ከችግር
ከፈተና ሲድን ይገኛል ።

የማያቋርጥ ጸሎት የሰውዬውን ተገዥነት
ይገልጣል ፤ ማለት በዚህ ዓለም የሚኖሩ የአ
ንዳንድ ጌቶች አሽከሮች ከባለሟልነታቸው
ወይም ጌታቸውን ከመውደዳቸው የተነሣ የጌቶ
ቻቸው ስም ከአንደበታቸው ሊለይ አይወዱም፤
ወይም ከነርሱ ጋር ሲነጋገሩ ቢውሉ አይጠግቡ
ትም ፤ እንደዚህም ሁሉ እውነተኛው ክርስቲ
ያን ከፈጣሪው ጋር በትክክል ሲናገር ሳይሰለች



ሳይመረር መሆን አለበት ። ከላይ እንደገለጽ
ኩት ሳይቻኩል፣ የምንግዴ ሳይሆን ፈጣሪውን
በእምነት ከፊቱ አድርጎ ይለምነው ይሰጠዋል፤
ሳያምን የምን ግዴ ቢለምነው ግን ምንም የሚ
ያገኘው ነገር የለም ፤ እንደዚህም ሁነው የጸለዩ
ምንም ያላገኙ ተስፋም የቈረጡ ብዙዎች ናቸው
እነዚህ ሰዎች ከምሕረቱ ከቸርነቱ ርቀው ተስፋ
ቈርጠው የቀን ጨለማ ወርሷቸው ይኖራሉ፤
ሲለምኑም ፈቃደ ሥጋቸውን ለመፈጸም እንጂ
ለበጎ ተግባር ለመንፈሳዊ ዓላማ አይለምኑም ፤
ስለዚህ ምንም ጥቅም እንደሌላቸው ይወቁ፤
በሃይማኖቱ ግን ይለምን ሳይጠራጠር ፤ ተጠራ
ጥሮ የሚለምን ነፍስ የምትመታውን የምትመ
ልሰውንም የባሕርን ሞገድ ይመስላል ። ለዚያ
ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ አንዳች የሚወስድ
አይምሰለው ። ሁለት ልብ ያለው ሰው በመን
ገዱ ሁሉ የጸና አይደለም» ( ያዕቆብ ፩፡፪) ሲል
መስክሮባቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

አሁንም ወደፈጣሪያችን ኑ እርሱንም እናመ ስግነው፤ችግራችንን ገልጠን እንንገረው፤እርሱ የለመኑትን የማይነሣ ፥ የነገሩትን የማይረሳ ፥ የማያጣጥል ሳያመነታ ቸል ሳይል ሳይውል ሳያድር የሚሰጥ አምላክ ነው ፤ እርሱ ምሕረቱ ለዘለዓለም ስጦታውም የማያቋርጥ የሆነ አም ላክ ነው ፤ ኑ እንለምነው ኑ እንማልደው እንቀ ድሰው ኑ አምልኮቱን ጌትነቱን ገልጠን እንን ገርለት ።

ተፈጸመ

ምስጋና ለእግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org